ላይ እንዲጣድ እና በጋለው ሳህን ላይ እርሷ እና ልጆቿ እዚያ ውስጥ እንዲጨመሩ አዘዘ። ይህንን ትእዛዝ የሰማችው ሴት ማድረጉንስ አድርግ ግን አንድ ነገር ግን እንድታደርግልኝ አፈልጋለሁ አለችው፣ እርሱም ምንድን ነው? ይላታል፣ እርሷም በማስከተል፡ ከገደልከን በኋላ የእኔን እና የልጆቼን አጥንት ሰብስበህ በአንድ ከፈን እንድትቀብረን አለች፣ እርሱም ቢሆን በእኛ ፍላጎት ነው አላት።

ፊርዓውንም ልጆቿ ወደ ጋለው ሳህን አንድ በአንድ እንዲጣሉ አዘዘ ፣ እናት በወላድ አንጀቷ የሚሆነውን ሁሉ እያየች ትዕግስቷ የሚደንቅ ነበር ፤ ልጆቿን ትቆጥራለች፣ ልጆቹም በፍርሃት ያለቅሳሉ፡ ይጮሃሉ፡ ከዚያም በእሳት ተቃጥለው ይሞታሉ፡ ነገር ግን ይህንን ሁሉ የምትመለከተው እናት ምንም ማድረግ አልቻለችም። የልጆቿን ጩኸት የምትሰማው እና ስቃያቸውን የምትመለከተው እናት አንጀት አልቻለም ፣ አቃታት እና ተስፋ ወደ መቁረጥ አጋደለች። የዚህን ጊዜ ታዲያ አላህ (ሱ.ወ) የሚጠባውን ሕፃን ልጇን አናገረው "እናቴ ሆይ አብሺራ፡ ታገሺ፡ በእርግጥም እውነትን ይዘሻል አለ።" በመጨረሻም አላህ ሆይ እስልምናዬን ተቀበለኝ እያለች ነበር ከእነ ልጆቿ እሳት ውስጥ የወረወራቸው።

ይህች እንስት ለሙስሊም ሴት ጥሩ የጥንካሬ እና የእምነት ተምሳሌት ተደርጋ ትወሰዳለች፣ አላህን የምታውቀው፡ የሚታወቅበት ድካ ድረስ ነበር፣ እምነቷን አጥብቃ ነበር የያዘችው ፣ በአላህ መንገድ ላይ የነበራት ትዕግሥት የሚገርም ነበር፣ ሊያስፈራሯት ሞከሩ፡ ወይ ፍንክች ከአቋሟ፣ በልጆቿ ስቃይ ተፈተነች ምንም ለውጥ የለም፣ በመጨረሻም ራሷን እጅግ አስደናቂ የሆነውን የመሥዋዕት፣ የትዕግሥት፣ የቤዛነት እንዲሁም ከአላህ ምሕረት ተስፋ ያለ መቁረጥ ምሳሌ ካደረገች በኋላ፡ የፊርዓውን ልጅ ተንከባካቢ እና ጸጉር አበጣሪ ከነ ልጆቿ መሥዋዕት በመሆን ይህችን ዓለም ተሰናበተች።

ነፍሷ እያንዳንዷ አማኝ ነፍስ ወደ ምትመኘው ትልቅ ተስፋ የተቆራኘች ምስኪን ሴት፣ ይህ ተስፋ የአላህን ውዴታ እና ጀነትን መጎናጸፍ ነው። ይህ ተስፋዋ ነበር ነፍሷ በፊርዓውን እና በጀሌዎቹ ስትቃጠል፣ የልጆቿን አሳማሚ የለቅሶ ድምጾች

እየለማች ፡ ወደኋላ እንዳታፈገፍግ፣ ተስፋ እንዳትቆርጥ፣ ተስፋዋ እንዳይሟጠጥ እንዲሁም ያንን መራራ ስቃይ በድል እንድትወጣው ያደረጋት። ግን ይህ እምነት ወደ አማኝ ነፍስ ዘልቆ ሲገባ የምሥራቹ በፍጥነት ይመጣል

..."እናቴ ሆይ ታገሺ፡ በእርግጥም በእውነት ላይ ነሽ!"...

♦♦♦◯♦♦♦

ዱዓእ

ኑ እስኪ አንዴ ይህን ሞቅ ያለ እና ፈዋሽ የሆነን ዱዓእ በአንድ ላይ እንበል። ምክንያቱም ይህ ዱዓ ጭንቀታችንን፣ ሀሳባችንን እንዲሁም ሀዘናችንን የምናስወግድበት መሳሪያ ስለሆነ ነው።

ዱዓውም እንደሚከተለው ይቀርባል፤

1. "ላኢላሃ ኢልለሏሁል ዓዚሙል ዓሊም፣ ላኢላሃ ኢልለሏሁ ረቡል ዓርሺል ዓዚም፣ ላኢላሃ ኢልለሏሁ ረብቢ ሰማዋቲ ወረቡል ዓርሺል ከሪም፣ ያሓዩ ያቀዩም ላኢላሃ ኢልላ አንተ ቢራሕመቲከ አስተገስ"

"ከታጋሹ እና ከአዋቂው አላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ከታላቁ የዓርሽ ባለቤት አላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ከሰማያት አምላክ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም። አንተ ሕያው የሆንክ ፈጣሪ፣ ከአንተ ሌላ አምላክ የለም፣ በምሕረትህ እርዳታን እሻለሁ።"

2. "አሏሁም ራሕመተከ አርጁ፣ ፈላ ተኪልኒ ኢልላ ነፍሲ ጠርፈተ ዓይኒ፣ ወአስሊሕ ሊ ሸእኒ ኩሊሂ፣ ላኢላሃ ኢልላ አንተ"

"አላህ ሆይ ምሕረትህን ተስፋ አደርጋለሁ፣ ለዓይን ጥቅሻ ያክል እንኳን አትተወኝ ጉዳዮቼንም ሁሉ አስተካክልልኝ፣ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም።"

3. “አስተግፊሩሏሁ ለዚ ላኢላሃ ኢልላ ሁወል ሐዩል ቀዩም ወአቱቡ ኢለይሂ”

“ከአላህም ምህረትን አለምናለሁ ከእርሱ ሌላ አምላክ የሌለ ህያው እና ቻይ ወደሆነው ወደርሱም አፀፀታለሁ።"

4. “ላኢላሃ ኢልላ አንተ ሱብሓነከ ኢንኒ ኩንቱ ሚነዚሊሚን”

"ጥራት ይገባህ፤ ካንተ ሌላ አምላክ የለም አኔም ከበደለኞች ነበርኩ።”

5. አሏሁም ኢኒ ዓብዱክ፤ ኢብነ ዓብዱክ፤ ኢብነ አማቱክ፤ ናሲየቲ ቢየዲክ፤ ማዲ ፊሑክሚክ፤ ዓድሉን ፊቀዷኡክ፤ አስአሉክ ቢኩሊ ኢስሚን ሁወ ለክ ሰመይተ ቢሂ ነፍሰክ፤ አው አንዘልተሁ ፊኪታቢክ፤ አው ዓለምተሁ አሐደን ሚን ኸልቂክ፤ አዊስተአሰርተ ቢሂ ፊዒልመል ገይቢ ዒንደክ፤ አን ተጅዓለል ቁርዓነ ረቢዐ ቀልቢ፤ ውኑረ ሰድሪ፤ ወዘሀበ ሃምሚ፤ ወጀላአ ሑዝኒ”

“አምላኬ አኔ ባሪያህ ነኝ፤ የባሪያህ ልጅ ነኝ፤ የሴት ባሪያህ ልጅም ነኝ፤ መርሳቴም በእጅህ ነው፤ በፍርድህም አጸናለሁ፤ በውሳኔዎችህም አስማማለሁ። ራስህን በሰይምክበት ሥምህ ሁሉ አለምንሃለሁ። በመጽሐፍህ ውስጥ ባወረድከው ሥምህ አለምንሃለሁ። ወይም ከፍጥረቶችህ ለአንዱ ባስተማርከውም አለምንሃለሁ። ቁርዓንን የቀልቤ ምንጭ፤ የልቤ ብርሃን፤ የጭንቀቴን መውጫ፤ የሃዘኔን ማስወገጃ አንድታደርግልኝ አንተ ጋር ባለው አና ምስጢር በሆነው ዕውቀትህ ባጋራኸው ሥም ሁሉ አጠይቅሃለሁ።”

6. አሏሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ሃሚ ወልሓዘን፤ ወልዓጂዚ ወልከሰል፤ ወልቡኽሊ ወልጅቡን፤ ወደልዒ ደይኒ ወገለበቲ ሪጃል”

“አምላኬ ሆይ ከጭንቀትና ከሐዘን፤ ከአቅም ማነስና ከስንፍና፤ ከመከራና ከፍርሃት፤ ከዕዳ ሸክምና በበላይህ ከመበደል በአንተ አጠበቃለሁ።”

7. “ሐስቡነሏህ ወኒዕመል ወኪል”

"አላህ በቂያችን ነው። ምን የሚያምር መመኪያ ነው?"

♦♦♦◯♦♦♦

ንሥር አሞራም ቢሆን ያው ዶሮ ነው

ነገርየው ቀደም ባለ ጊዜ ይነገር የነበረ ታሪክ ነው ይባላል። ተራራ ላይ በበቀለ ትልቅ ዛፍ ላይ ጎጆዋን ቀልሣ የምትኖር ንሥር ነበረች፤ በጎጆውም ላይ አራት እንቁላሎች ነበሩ፣ አደገኛ የመሬት መንቀጥቀጥ በድንገት ይከሰትና ዛፉ በሚወዛወዝበት ወቅት አንድ እንቁላል ከጎጆው በመወደቅ፣ እየተንከባለለ ዶሮዎች የሚራቡበት ስፍራ አካባቢ ይደርስል፣ በቦታው የነበረች እናት ዶሮም እንቁላሉን መጠበቅ እና ተንከባከቦ እስኪፈለፈል ድረስ የማቆየት ኃላፊነት እንዳለባት ይሰማት እና እስኪፈለፈል ለማሳደግ ትወስናለች።

ከዕለታት አንድ ቀን ይኸው እንቁላል ይፈለፈል እና አንድ የሚያምር የንሥር አሞራ ተፈጠረ፣ ግን ይህ የንሥር አሞራ እንደማንኛውም ዶሮ ማደግ ይጀምራል፣ እናም ራሱን ዶሮ እንደሆነ አድርጎ እየተረዳ ማደጉን ቀጠለ፣ አንድ ቀን በእርሻው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲጫወት ፣ የንሥር አሞራዎች ስብስብ በኩራት በሰማይ ላይ ሲበርሩ ይመለከታል። የዚህን ጊዜ ነበር እንደነዚህ አሞራዎች ከፍ ብሎ መብረር ቢችል የተመኘው፣ ነገር ግን ዶሮዎቹ "አንተ እኮ ዶሮ ነህ እንጂ አሞራ አይደለህም፣ ጭራሽ ከፍ ብለህ በሰማይ ላይ ልትበርም ያምርሃል እንዴ" እያሉ መሳቂያ መሳለቂያ አደረጉት: በመጨረሻም ከፍ ብሎ የመብረር ሀልሙን ተስፋ በመቁረጥ አቆመ፣ ብዙም ሳይቆይ ረጅም ዕድሜውን በሙሉ እንደ ዶሮ ከኖረ በኋላ ሞተ።

ይህ ንሥር አሞራ በዶሮዎች መካከል በመፈጠሩ ምክንያት ዶሮ እንደሆነ ነበር ያመነው፣ እንደሚታወቀው ዶሮዎች ወደ ሰማይ ከፍ ብለው መብረር አይችሉም፣ ለዚህም ነበር የመብረሩን ጉዳይ ትኩረት ያልሰጠው።

እንግዲህ ከታሪኩ የምንረዳው ነገር ቢኖር፣ አንድ ሰው በአሉታዊ መልኩ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሆኔታዎችን አምኖ በተቀበለው ልክ አስረኛ ሆኖ እንደሚቀር ነው፤ ስለዚህ ንሥር አሞራ ከሆንክ እና ከፍ ብሎ የመብረር ሀልም ካለህ ፡ ሀልምህን ብቻ ተከተል፣ እንደ ዘመዶችህ፡ እንደ ጓደኞችህ እና እንደ ወንድሞችህ እንዳትሆን ለሚያፈዙብህ ዶሮዎች ጆሮህን አትስጥ።

እናም ስለራስህ ያለህ የግል እይታህ እና የምኞትህ ግዝፈት ከውድቀት ነፃ በመሆን ስኬታማነትህን የምትወስንበት መሆኑን እወቅ! ራስህን ፈልገህ በማግኘት፣ ለራስህ ያለህን ግምት እና አመለካከት ከፍ ማድረግ ይኖርብሀል፣ ይህ ነው የስኬት መንገድህ፣ እናም ጓደኝነትህን ውሳኔህን ከሚያጠናክር ሰው ጋር ማድረግህን አትዘንጋ።

- በስኬት ሰማይ ላይ ከፍ ብለህ መብረር ከፈለግህ፣ ሀልመኛ ሁን፣ ተግተህ ሥራ
- ንሥር አሞራ ቢሆንም ዶሮ እንደሆነው ከመሆን ራስህን ጠብቅ...

ጥራት ይገባው እና አላህ (ሱ.ወ) እኮ እሱን በመገዛት እና በመታዘዝ ላይ እንድታውላቸው እና እንድትመራመርባቸው የሚያገለግሉ ለቁጥር የሚያዳግቱ ችሎታዎችን እና ጉልበቶችን የሰጠህ እና የመረጠልህ ጌታህ ነው። በአግባቡ ከተጠቀምክበት ደግሞ በዱኒያም በአኼራም ስኬታማ እንደምትሆን ቃል ገብቶልሀል።

> <u>መልዕክት 23፡</u> ስለዚህ በስኬት ሰማይ ላይ ብረር... የተሰጠህን ጉልበት እና ችሎታ በአግባቡ ተጠቀም... እንዲሁም ተስፋ ከመቁረጥ እና ከፍራቻ በሚመነጩ ለውድቀትህ ምክንያት በሚሆኑ ነገሮች ሁሉ አትረበሽ።

♦♦♦◯♦♦♦

የማይቻለውን ማሸነፌያው "በራስ መሥራት"

ሼኽ ሱለይማን ቢን ዓብዱልዓዚዝ አር-ራጂሒ፣ 'ሀ' ብሎ አንቅስቃሴ የጀመረው ምንም ሳይኖረው ነበር፣ ይህ ሰው ስመ-ጥር የንግድ ሰዎች የካርታ ዝርዝር ውስጥ አስኪካተት ድረስ፣ ተስፋ መቁረጥ የሚባል ነገር በልቡ ውል ብሎበት አያውቅም። ትንሹም ትልቁም ከስተት ሁሉ ከአላህ ነው፤ እውነት ነውም፤ ብሎ ያምናል፣ አላህም እውነት ብለሀል ይለዋል። በአንድ ወቅት፣ በአንድ ለሕዝብ ክፍት በሆነ መድረክ ላይ በመገኘት የሕይወት ታሪኩን የኋሊት ማብራራቱን ቀጠለ። እቃ አመላላሽ በመሆን አንድ ሪያል እየተከፈለው ይሠራ እንደነበር እና አሁን ላይ በተለያዩ የሥራ ድርጅቶቹ እስከ 15 ሺህ የሚደርሱ ሠራተኞችን በማስተዳደር ላይ እንደሚገኝ ገለጸ።

እስኪ የትግሉን ጉዞ በትህትና እና በመተማመን ሲተርክ ልብ ብላችሁ አድምጡት... አል-ራጂሒ እንዲህ ይላል፣ የኔ አስተዳደግ፣ እዚህ አገር ሌሎች ወጣቶች ከሚያድጉበት የተለየ አስተዳደግ አልነበረም። የትምህርት ዝግጅቴም ቢሆን ከአንደኛ ደረጃ ሰርተፍኬት የዘለለ ሌላ ምንም ዓይነት የተለየ የትምህርት ደረጃ አልነበረኝም፣ በወቅቱ ነጋዴዎችም ከሺህ እና ከሁለት ሺህ ሪያል በላይ አልነበራቸውም፣ ይህ ማለት በዛ ወቅት የገንዘብ እጥረትም ነበረብኝ፣ እናም ጉዞዬን አንድ ብዬ የጀመርኩት አንድ ሪያል እየተከፈለኝ፣ እቃ ተሸካሚ እና አሳላፊ በመሆን ነበር፤ ይህ ደግሞ እጄን ለማንም አንዳልዘረጋ በኩራት እና በወኔ ለራሴ መንገር ጀመርኩ፣ ከዚያ በኋላ በለጋ ዕድሜዬ መሥራቴን ተያያዝኩት። ሥራዬም ወርሃዊ ሆነ፣ ሪያሎችም ይከፈለኝ ጀመር። በዚህም አላቆምኩም ከየቤቱ አመድ እየሰበሰብኩ በማምጣት፣ አመዱን ከጭቃ ጋር ቀላቅዬ በመለወስ መስጂድ ለመሥራት 10 ሪያል እንዲከፈለኝ ተስማማሁ ሆኖም ግን የቤቶቹ ባለቤቶች ወጥ ቤታቸውን (ኪችናቸውን) እስካላጸዳሁ ድረስ አመድ ሊሰጡኝ ፍቃደኛ አልነበሩም። ከዚያ በኋላ ወደ አብሳይነት ሙያ ተዛወርኩ፣ የተዋጣለት አብሳይም ሆንኩኝ ምሥጋና ለ አላህ ይሁን እና፤ የዚህን ጊዜ ነበር ወንድሜ ሷሊህ አር-ራጂሒ በ1965

የራሱ ድርጅት ውስጥ በ1ሺህ ሪያል ተቀጥሬ አንድሠራ ያደረገኝ። በዚህ አጋጣሚ ነበር ወደ ሥራው ዓለም በደንብ የተቀላቀልኩት።

በሉ እንግዲህ ሼኽ ሱለይማን ስለ ስኬታቸው ሲተርኩ በጥሞና አድምጡ... በአላህ ፈቃድ የምተገብረው፤ ለአፍታም ቢሆን ውልፍት የማልልበት የሥራ እቅድ እና መርሐግብር ነበረኝ፤ የሥራው ዘርፍ ምንም ዓይነት ቢሆን፣ በመለዋወጫ፣ በአርሻ፣ በኢንዱስትሪ፣ በዶሮ እርባታ ወዘተ በመሳሰሉት... በሥራ ቦታችን ላይ ቀድሞ በመገኘት እና ዘግይቶ በመውጣት የሚስተካከለኝ አልነበረም፤ የሥራው ባላቤት ደግሞ ለሥራው ፍላጎት ያደረበት መሆን ይገባዋል። ይህ ደግሞ የአር-ራጂሒ ድርጅት የተቋቋመበት ዓላማ ነበር። ከፈጅር ሰላት በፊት፡ ጎህ ሳይቀድ ነበር ሳንድዊቼን ይዤ ከቤት የምወጣው፡ ይህ ማለት ከሠራተኞች ሁለት ሰዓቶችን ቀድሜ ነበር የምገባው ማለት ነው፤ በዚህ ሁኔታ የንግድ ሥራዬ መሠረት እስኪጥል እና በደንብ እስኪቋቋም እሠራ ነበር።

♦♦♦◯♦♦♦

ተፋኡል

አነስ ኢብን ማሊክ ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸው እና ከመልዕክተኛው ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይዘው ባስተላለፉት መልዕክት እንዲህ ይላሉ "እኔን የሚያስገርመኝ ነገር ጠላትነትም በኮከብ ቆጠራ ማመንም አይደለም፤ ተፋኡል ነው"። ይህን ባሉ ጊዜ ተፋኡል ምንድን ነው? ተብለው ተጠየቁ። አነስም ተፋኡልማ መልካምን ከውስጥህ ማሰብ ነው በማለት ይመልሳሉ።" በሌላ ዘገባም ተፋኡል የሚያስደንቀኝ ነገር ሲሆን መልካም ነገር ከውስጥህ ማሰብ ማለት ነው" ብለዋል።

> <u>መልዕክት 24፡</u> በመልካም ነገር ተስፋ ማድረግ፣ የጠንካሮች እና አቋም ያላቸው ሰዎች መገለጫ ዘይቤ ነው። በኮከብ ቆጠራ ማመን ማለት ደግሞ የጨለምተኞች ተስፋ ነው። ነገሮችን

አጨልሞ እና አደብዝዞ ማየት ሲሆን፣ ይህም የደካሞች፣ የተሸናፊዎች እና የችግር ጠሪዎች መገለጫ ዘይቤ ነው።

♦♦♦◯♦♦♦

አስተንትን፣ በፈጣሪህም ተመካ

- **አሁንን ኑር፡** አብዛኞቹ የጭንቀት ዓይነቶች ስላለፈው በመቆጨት ወይም የወደፊቱን በመፍራት የሚመጡ ስለሆነ ያለፉትን ልምዶች በመጠቀም ለወደፊት ሊከሰቱ ለሚችሉ ነገሮች በሚግገባ አቅድ።
- **ፍርሃትን ተጋፈጥ፡** ብዙ ፍርሃቶች እውነተኛ አይደሉም፣ በችግሮች መካከል ደፋር ሁን፣ በጣም የከፋውን ለመቀበል ራስህን አዘጋጅ፣ ከዚያ ይህ ነገር መጥፎ አይደለም በማለት ሥራ፣ ይህን ሁሉ ስታደርግ እያስተነተንክ ሬታህን መፍራትን እንዳትዘነጋ።
- **እውነታውን ተቀበል፡** ያንተ ራዕይ እውነታህ ነው፣ የሚያስጨንቀህን እወቅ ፣ ከዚያ በደንብ አስተንትን፣ ከዚያ ተመካከረህ ኢስቲሻራን (ምርጫህን) ተጠቀም ፣ ከዚያ ውሳኔህን አስቀምጥ በወሰንከው ነገርም እንዳትቆጭ።
- **የጭንቀትን፣ የተስፋ መቁረጥን እና የፍራቻን አደገኛነት አስታውስ፡** አካላዊ በሽታዎችን ማለትም የልብ በሽታን፣ ጭንቀትን፣ የሆድ በሽታን፣ የደረት በሽታን፣ የጀርባ ህመምን፣ ኢንፌክሽንን (ደዌን) አቅመ ቢስነትን አንዲሁም ከሥነ-ልቦና ጋር የተያያዙ በሽታዎችን አስታውስ።
- **የመርሳትን ጥበብ ተማር:** ለመኖር ሲባል ነገሮችን እንዴት መርሳት እንደምትችል ተማር፣ ሁሌም ነገሮችን የሚያወግዝ ማሽን መሆንን አትቀበል፣ ለሚያልፍ ነገር እያንዳንዱ ከስተት ላይ ድርቅ አትበል፣ ነገሮች በራሳቸው ዛቢያ እንዲከናወኑ አድርግ፣ ስቃይ እና ብስጭትን የሚጨምሩ ከስተቶችን መቀነስ ላይ በርታ።
- **ፈገግ በል፡** ፈገግታ ከብዙ ጥረት በኋላ ለሚገኘው ደስታ ዋነኛው እና የመክፈቻ ቁልፍ ሲሆን የዚህ ጥረት ምልከቱ እና ማስረጃው ፈገግታህ ነው። ፈገግታህም ተጽፎ የተቀመጠ ምጽዋት ነው።